# ለአዋሽ ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ
# የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምርጫ ሂደትና መስፈርቶች ለማሳወቅ የወጣ ማስታወቂያ

የባንካችን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 መሠረት ህዳር 13 ቀን 2018 ዓ.ም. በስካይላይት ሆቴል በሚካሄደው የባንኩ 30ኛ መደበኛ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይካሄዳል። የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫውም በዕለቱ በሚመረጠው የዳይሬክተሮች ቦርድ ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ አማካይነት የሚከናወን ሲሆን 1/3ኛ እጩ ቦርድ አባላት ወሳኝ ድምፅ በሌላቸው ባለአክሲዮኖች፤ እንዲሁም 1/3ኛ እጩ ቦርድ አባላት ደግሞ በሁሉም ባለአክሲዮኖች በዕለቱ ተጠቁመው ለምርጫ የሚቀርቡ ሲሆን ገለልተኛ የሆኑ 1/3ኛ እጩ ቦርድ አባላት ደግሞ በዳይሬክተሮች ቦርድ ተመልምለው በጊዜያዊ የቦርድ አስመራጭ ኮሚቴው አማካይነት ለምርጫ ይቀርባሉ።

ስለሆነም ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት እጩ ሆነው መቅረብና መመረጥ የሚችሉት የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆን የሚገባቸው መሆኑን ባንኩ በአክብሮት ያሳውቃል።

1. **ከባለአክሲዮኖች ለሚጠቆሙና ለሚመረጡ እጩ የቦርድ ዳይሬክተሮች፡-**
   1.1. ቢያንስ ለሁለት ዓመት የባንኩ ባለአክሲዮን የነበረ/ች፤
   1.2. ባንኩን በቦርድ አባልነት ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነ/ች፤
   1.3. የሌላ ማንኛውም ባንክ ሠራተኛ ያልሆነ/ች፤
   1.4. ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ያለው/ላት፤
   1.5. በቢዝነስ ማኔጅመንት፣ በባንኪንግ እና/ወይም ፋይናንስ፣ በሂሳብ አያያዝ፣ በሕግ፣ ሪስክ ማኔጅመነት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በመሳሰሉት የትምህርት ዘርፎች ቢያንስ ሰባት (7) ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ላት፤
   1.6. የሌላ ፋይናንስ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ያልሆነ/ች፤
   1.7. ታማኝ እና ሀቀኛ የሆነ/ች እንዲሁም እና መልካም ዝና እና ሥነ-ምግባር ያለው/ላት፤
   1.8. የህዝብ ጥቅም ለመጠበቅ የወጣ ህግ በመተላለፍ በማጭበርበር፣ እምነት በማጉደል፣ ተከስሶ/ሳ በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሠጥቶበት/ባት የማያውቅ/የማታውቅ፤
   1.9. በራሱ/ሷ ወይም እሱ/ሷ በዋና ባለቤትነት የያዘው/ችው ድርጅት በሚመለከት ለሕዝብ መገለጽ ያለበትን መረጃ ደብቆ/ቃ የማያውቅ/ታውቅ፣ ሃሰተኛ የሂሳብ መግለጫ አቅርቦ/ባ የማያውቅ/ታውቅ፣ የተቆጣጣሪ አካላትን ውሳኔ ላለመቀበል ወይም ላለመገዛት እምቢተኛ ሆኖ/ና የማያውቅ/ታውቅ፣
   1.10. እራሱ/ሷ ወይም እሱ/ሷ በዋና ባለቤትነት የያዘው/ችው ድርጅት ተመርምሮ እምነት በማጉደል፣ በማጭበርበር ወይም በተመሳሳይ ጥፋት በተቆጣጣሪ አካል፣ በፍ/ቤት ወይም ትራይቡናል የዲሲፕሊን እርምጃ፣ ዕገዳ ወይም ቅጣት ተላልፎበት/ባት የማያውቅ፤
   1.11. በራሱ/ሷ ወይም ዳይሬክተር ወይም ዋና ስራ አስፈጻሚ ወይም ስራ አስፈጻሚ በሆነበት/ችበት ድርጅት ላይ የመክሰር ክስ ያልቀረበበት/ባት ወይም የኪሳራ ውሳኔ ያልተሰጠበት/ባት፣ በኪሳራ ምክንያት ንብረቱ/ቷ ለዕዳ ማቻቻያ ያልተወሰደበት/ባት፣
   1.12. እራሱ/ሷ ወይም ዳይሬክተር ወይም ዋና ስራ አስፈጻሚ ወይም ስራ አስፈጻሚ የሆነበት/ችበት ድርጅት የባንክ ወይም ሌላ ብድር ወይም ታክስ ባለመክፈሉ/ሏ ምክንያት ንብረቱ/ቷ በሃራጅ ያልተሸጠበት/ባት፣
   1.13. ታክስ ባለመክፈል ተከሶ/ሳ ጥፋተኛ ያልተባለ/ች፤

1.14. እራሱ/ሷ ወይም ዳይሬክተር ወይም ዋና ስራ አስፈጻሚ ወይም ስራ አስፈጻሚ የሆነበት/ችበት ወይም ባለቤት የሆነበት/ችበት ድርጅት የተበደረውን ገንዘብ ባለመክፈሉ/ሏ ብድሩ ባለፉት ሁለት አመታት ውስጥ ጤናማ ያልሆነ ምድብ ውስጥ ገብቶበት/ባት የማያውቅ፤

1.15. ባለአክሲዮኑ/ኗ አክሲዮን የገዛበትን/ችበትን ገንዘብ ያገኘው/ችው ከከሰረ ሰው ወይም በአስተዳደር ችግር ምክንያት ኪሳራ ካጋጠመው ሰው ያልሆነ ወይም ገንዘቡን ያገኘው/ችው በማጭበርበር ወይም በህገ-ወጥ መንገድ ያልሆነ፤

1.16. ባለአክሲዮኑ/ኗ የአክሲዮኑ ባለቤት በሆነ/ች ጊዜ የነበረው/ራት የሀብት መጠን ከአክሲዮኖቹ ዋጋ በላይ የነበረ፤

1.17. በቂ ስንቅ/ገንዘብ ሳይኖረው/ራት ቼክ ሰጥቶ/ታ ሂሳቡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ያልተዘጋበት/ባት።

1.18. በሌሎች ከአራት በበለጡ ተቋማት ውስጥ የቦርድ አባል በመሆን በማገልገል ላይ የማይገኝ/የማትገኝ፤ እንዲሁም

1.19. ከዚህ በፊት በንግድ ማኅበር አደራጅነት፣ ዳይሬክተርነት፣ ሥራ አስኪያጅነት፣ ተቆጣጣሪነት፣ ኦዲተርነት ወይም በሌሎች የአመራር ኃላፊነቶች ላይ ተመድበው ሲሰሩ ከኃላፊነታቸው ጋር በተያያዘ ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ በእምነት ማጉደል፣ በስርቆት ወይም በውንብድና ወይም ለቦርድ አባልነት ብቁ በማያደርግ ተመሳሳይ ወንጀል ጥፋተኛነታቸው ያልተረጋገጠ፤ መሆን ይገባቸዋል።

1.20. የሚጠቆመውና የሚመረጠው የቦርድ አባል ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ድርጅቱን በመወከል በቦርድ አባልነት የሚያገለግለው ሰው ማንነት መታወቅና ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል።

1.21. ከላይ የተዘረዘሩት መስፈርቶች ድርጅቶችን ወክለው በሚመረጡት የቦርድ አባላት ላይም ተፈፃሚነት አላቸው።

2. <u>ለገለልተኛ እጩ የቦርድ ዳይሬክተሮች፡-</u>

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና በሕግ የተቀመጠውን መስፈርቶች የሚያሟሉ ገለልተኛ እጩ ዳይሬክተሮች በዳይሬክተሮች ቦርድ ተመልምለው በአስመራጭ ኮሚቴው አማካይነት ለምርጫ የሚቀርቡ ይሆናል።

<u>ማሳሰቢያ፡-</u>

- አንድ ባለአክሲዮን እራሱን በእጩነት መጠቆም ይችላል፤
- ቢያንስ ሁለት ሴቶች በቦርድ አባልነት መመረጥ አለባቸው፤
- የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት በቦርድ አባልነት መመረጥ አይችሉም፤
- ሶስት ዓመት ያገለገሉ ነባር የቦርድ አባላት በድጋሚ መመረጥ ይችላሉ፤
- የባንኩ የቦርድና የማኔጅመንት አባላት እንዲሁም የባንኩ ሠራተኞች ባለአክሲዮኖችን ወክለው ድምፅ መስጠት አይችሉም፤
- በዕለቱ አምስት አባላት ያሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ የሚመረጥ ሲሆን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትና የባንኩ ሠራተኞች የኮሚቴው አባል ሆነው መመረጥ አይችሉም።
- ከሚመረጡት የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባላት ቢያንስ ሁለቱ ተደማጭነት የሌላቸው ባለአክሲዮኖች መሆን ይኖርባቸዋል።

አዋሽ ባንክ አክሲዮን ማህበር